# ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ለሕዝብ የቀረበ ጥሪ

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከጨበጠበት ከ1983 ዓ. ም ጀምሮ አገሪቱን ለራሱ በሚያመቸው መንገድ በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ ለአለፉት 18 ዓመት ሲገዛ ቆይቷል፤ ይህን በመከፋፈል ላይ የተመሠረተ አስተዳድር የሚቃወሙትን ዜጎች በመወንጀል፣ በማሳደድና አገር ጥለው እንዲሰደዱ ከፍተኛ ጫና አድርጓል::

ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ቀን ጀምሮ ከራሱ ሰዎች በስተቀር ለአንተ አንድም ቀን እድል ገጥሞህና በምታደርገው እርምጃ ሁሉ ቀንቶህ አያውቅም፤ ይህ በመሆኑም ድሮ የነበረህን የውስጥ ደስታና የእርስ በእርስ ፍቅር አጥተህ በዘርና በጎሳ በመለያየት በመናቆር ላይ ነህ፣ ሰው ሰራሽ በሆነው የኑሮ ውድነትም በመጠበስ ላይ ትገኛለህ።

የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፍትህ የጎደለው ከመሆኑ የተነሳ ጥቂት አፍቃሬ ኢህአዴግ የሆኑ ግለሰቦችን በአንድ ጀምበር ሚሊየነር ሲያደርግ ብዙ ዜጎችን ደግሞ ወደ ድህነት አዘቅት ውስጥ ይወረውራቸዋል
የኢህአዴግ መንግሥት በየጊዜው የሚያወጣቸው ብሔራዊም ሆነ ክልላዊ ፖሊሲዎቹ ለህገርም ሆነ ለሕዝብ ጥቅም ታስቦ ሳይሆን ለገዢው ፓርቲ የፖለቲካ ትርፍ እንዴት እንደሚያስገኝ በታሳቢነት ተይዞ አይደለምን?

ልጆችህ በአገራቸው ላይ ሥራ በማጣታቸው የተነሳ ወደ ተለያዩ የአረብ አገራት ለባርነት በመሰደድ ላይ ባሉበት በአሁኑ ወቅት የኢህአዴግ መንግሥት አናጺና ግንበኛ ከፓኪስታን፣ የእንጨትና የብረት ሰራተኛ ከቱርክና ከቻይና በማምጣት የኢኮኖሚ ወረራ እንዲደርስብህ አድርጓል:: በዓለም ላይ ለአገርና ለሕዝብ የሚቆረቆር መንግሥት ያላቸው አገሮች የሚያደርጉት ሥራውን የሚያከናውን ዜጋ በአገሪቱ እስካልጠፋ ድረስ ኮንትራክተሮችም ሆነ የእርዳታ ድርጅቶች ሠራተኛ ከውጭ ማምጣት አይችሉም አይፈቀድላቸውምም፤ ይሁን እንጂ የእኛ መንግሥት በሥልጣን ላይ የሚያቆየውን የፖለቲካ ትርፍ በማሰብም ሆነ በሌላ ስውር ምክንያት ከእንደዚህ ያለ የኢኮኖሚ ብዝበዛ ጥቃት ሊጠብቀን አልቻለም ፈቃደኛም ሆኖ አልተገኘም

## አንተ የንግዱ ሕብረተሰብ ሆይ!

በነጻነት ተንቀሳቅሰህ በመወዳደር እንዳትሰራ እንደ ቀረጥ ግብር፣ ፈጣን አገልግሎትና መረጃ በመስጠቱ ሒደት ላይ ብዙ ፖለቲካዊ ማነቆዎች ይጣሉብሃል አድልኦም ይፈጸምብሃል:: ለእነርሱ ሰዎች አስፈላጊው መረጃ አስቀድሞ ስለሚሰጣቸው የፋይናንስም ሆነ የአዕምሮ ዝግጅት ያደርጋሉ፤ በዚህ የተነሳም ጥቂቶቹ በሀብት ሲጥለቀለቁ ብዙሀኑ ከስረህ ከገበያው ትወጣለህ።

በ1997 ዓም በተደረገው ብሔራዊ ምርጫ በነጻነት ይመራኛል ብለህ ያመንክበትን ፓርቲ በመምረጥህ የተነሳ የተከራየኸውን የመንግስት ቤት ተነጥቀህ፣ በሥራህ ላይ ዙርያ ገባ የሆነ ደባ ተፈፀመብህ። የገዥው ፓርቲ የንግድ ድርጅቶች ተቋቁመው በአበዳሪነት፣ ባስመጪና ላኪነት፣ በጅምላና ችርቻሮ ንግድ እንዲሰማሩ ተደርጎ ቢሮክራሲያዊ እንቅፋት እንዳይገጥማቸው፣ የቀረጥና ግብር ውጣ ውረድ እንዳያስቸግራቸው፣ የካፒታል እጥረት እንዳይደርስባቸው የመረጃ እጥረት እንዳይኖርባቸው ሁሉ ነገር ተመቻችቶላቸዋል። በአንፃሩ አንተ ፍታሀዊ ባልሆነ ግብርና ቀረጥ ጫና፣ በቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረድ፣ በፋይናንስ እጥረትና በሙስና ወዘተ ሁለገብ እንቅፋት እንዲገጥምህ እየተደረገ ከገበያ እንድትወጣ ተደርገሃል። ነፃ ገበያ ይሉ ነገር ደብዛው በመጥፋቱ የተነሳ የሚያገለግለው ለአፍቃሬ ኢህአዴጎች ብቻ ነው። በየሄድክበት መሥሪያ ቤት ሁሉ ጉዳይ ለማስፈፀም ያለሙስና ማለፍ የማትችልበት ሥርዓት ሰፈነ። ያለሙስና የማይንቀሳቀሱ ባለሥልጣናት ሰራተኞች በጓዳ ላይ ቆመው አንተን የሙስና ተጠያቂ እያደረጉህ ነው። ታዲያ እንደዚህ ፍትሕ በጎደለው ውድድር ውስጥ ገብተህ በገበያው ውስጥ በዘላቂነት መቆየት ትችል ይመስልሃል? ካልተደራጀህና ካልተባበርክ ይህን የተቀነባበረ ሴራ፣ ዘረፋና ውድመት ልትገታው አትችልምና በመተባበር ከመኢአድ ጋር ለለውጥ ተነስ።

## ምሁሩ ሆይ!

በተለይ አንተ ለመደራጀት ብዙ እንቅፋቶች እንዳሉብህ ይታወቃል። ከተማዋ የፖለቲካ ሁሉ መንተክተኪያ የዓለም ትኩረት ማረፊያ በመሆኗ ገዥዎችህ በአካባቢህ በሚካሄደው እንቅስቃሴ የፖሊቲካ ንቃትህ ከፍተኛ እንደሆነ ስለሚያስቡ አንተ ላይ ያነጣጥራሉ። የገዥው ፓርቲና የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳ፣ የስለላ መረቦችና የልዩ ታጣቂዎች ጫና፣ በንብረትህና በሥራህ ላይ ሊሰነዘር የሚችለው ጥቃት ሁሉ እስከዛሬ ላለመደራጀትህ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ከነሱ ውጭ ብትደራጅ በይፋ ባይከለክሉህም ስውር ክትትላቸውም አስቸግሮህ ሊሆን ይችላል ግን ይህን ፈርቶ እስከመቼ መኖር ይቻላል? አሁን ግን በሰላማዊ ትግልህ ኢህአዴግ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ከማያደርስበት ደረጃ ላይ አድርሰኸዋል በቅርቡ እንደሰማኸው በማንኛውም ዜጋ ላይ የፖለቲካ ተጽዕኖ ላለማድረስ ቃል ገብቶ የውጭ መንግሥታት ተወካዮች በታዛቢነት በተገኙበት ፊርሞ በማህተም አረጋግጧል፣ ስለዚህ በሥራህም ሆነ በጥቅምህ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ወይም ጉዳት እንደማያደርስብህ በሙሉ ልብ እናረጋግጥልሃለን።

የተማርከውና የብዙ ዓመታት የሥራ ልምድ ያለህ ጠቃሚ ዜጋ ሆነህ ሳለ በነጻነት በመንቀሳቀስ ሰርተህ በተረጋጋ ሁኔታ ቤተሰብህን እንዳትመራ የኢህአዴግ አባል ለመሆን ፈቃደኛ ካልሆንክ በተለያዩ ምክንያቶች ከመደበኛ ሥራህ እንድትፈናቀልና ለችግር እንድትጋለጥ ያደርጉሃል:: ኢህአዴግ እየተገበረው ያለው መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ (Business Processing & Reengineering/ BPR) ለኢህአዴግ ለሚያጎበድዱ መሾሚያ ሲሆን የኢህአዴግን የተሳሳተ ፖሊሲ ለሚቃወሙ ደግሞ የደረጃ እድገት መከልከያና ከሥራ መፈናቀያ ዘዴ ሆኗል:: ታዲያ በአገርህ ላይ አእምሮህ ያሻውንና ለአገርህ ይጠቅማል ብለህ ያሰብከውን መፈጸም ካልቻልክ የመማር ውጤቱ የት ላይ ይሆን? የመማር ውጤቱስ ለውጥ ማምጣት አይደለምን?
የኢህአዴግ መንግሥት የተሻሉ መምህራንን በስበብ አስባቡ እያባረረ እውቀት፣ ችሎታና ብቃት የሌላቸውን አፍቃሬ ኢህአዴጎች በመተካት ለ18 ዓመታት የትምህርቱን ጥራት በማዳከም አንድ ትውልድ ከገደለ በኋላ ምርጫ ሲደርስ እንደሚያደርገው ሁሉ ከመስከረም ወር 2002 ዓም ጀምሮ የትምህርት ጥራት እንደሚያመጣ በማስመሰል በቁጥጥሩ ሥር ባለው የመገናኛ ብዙሀን ሲለፍ ይሰማል::

ጠቅላላ የትምህርቱ ፖሊሲ ቀረጻ ለኢህአዴግ የፖለቲካ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል በካድሬዎች ቁጥጥር ሥር በመውደቁ የተነሳ ጎበዝ ተማሪ የኢህአዴግ አባል ካልሆነ በአገሩ ላይ በውጤቱ መሠረት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግባት በማይችልበት አገር፣ የትምህርቱ ጥራት ሃይል ለሆኑት መምህራን ሙያዊ አክብሮትና ፍቅር እንዲሁም አስፈላጊው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጥበቃ በማይደረግባት አገር እውን የትምህርት ጥራትም ሆነ የአገር እድገት ሊመጣ ይችላልን? ፍርዱን ችግሩን ሁሉ በመጋፈጥ ላይ ላለኸው ለአንተ እንተወዋለን።

ዛሬ ወጣቶችን በወጣት ፎረም፣ ሴቶችን ደግሞ በሴቶች ፎረም በማደራጀት ነጻ ሕሊናቸውን በመሸጥ የኢህአዴግ የፖለቲካ ጀሌዎችና ደጋፊዎች እንዲሆኑና ኢህአዴግንም እንዲመርጡ በመወትወት ላይ ይገኛል:: መኢአድ ለእነዚህ ዜጎች የሚመክረው ይህ የሚረጨው ገንዘብ የኢህአዴግ ሳይሆን የአገራችን ሀብት ስለሆነ ገንዘቡን ተቀበሉና ተጠቀሙ፣ አደጋ ያመጣብናል የምትሉ ከሆነ ደግሞ ከአንገት በላይ የኢህአዴግ ደጋፊ ምሰሉ ነገር ግን በምርጫው ወቅት ተሳስታችሁ ኢህአዴግን በመምረጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥቃይና የመከራ እድሜ እንዳታራዝሙ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጉ!
ከዚህ በመነሳት ሕብረ ብሔራዊ የሆነው ፓርቲ መኢአድ በአገሪቱ ውስጥ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ቢሮዎችን በመክፈት ዜጎችን በእኩልነት የማያሳትፈው የኢህአዴግ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ፖሊሲ እንዲወገድ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል:: በአዲስ አበባም ቢሆን በሁሉም ክፍለ ከተሞችና በሥራቸው በሚገኙ ቀበሌዎች ሕዝቡን አደራጅቶ በግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ለሚደረገው ብሔራዊ ምርጫ እራሱን አዘጋጅቶ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፣ አንተም ሳትዘገይ የትግሉ አካል እንድትሆን ጥሪውን ያስተላልፋል።

## አገር ተረካቢ የሆንከው ወጣቱ ሆይ

እስቲ የራስህንና የቤተሰብህን ሁኔታ አስብ፣ በኢህአዴግ የተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት ታናናሽ ወንድሞችህና እህቶችህ ጠግበው ሳያድሩ፣ መልካም የሆነ የትምህርት ዕድል ተነፍጓቸው ቤት ሲውሉ፣ ከሰውነት ወጥተውና ክብራቸውን አጥተው፣ ማንነታቸውን ረስተው የበታችነት በመንገስ ላይ መሆኑ በጣም ያሳዝናል:: ይህ በሽታ ለልጅ ልጆችህ እንዳይተላለፍ ኢህአዴግን በሰላማዊ መንገድ በመታገል ቋሚ የሆነ መፍትሔ ልትፈልግለት ያስፈልጋል።

በበዘርፈ ብዙ ችግር ላይ ያሉ ቤተሰቦችህ አስተምረውህ በተቃራኒው በውጤትህ መሠረት ወደ ከፍተኛ ትምህርት እንዳትገባ የኢህአዴግ አባል ካልሆንክ የሚል ማዕቀብ ሲጣልብህ፣ ዲግሪና ከዚያም በላይ ማዕረግ ተሸክመህ የኢህአዴግ አባል ካልሆንክ በሚል ሰንካላ ምክንያት በአገርህ ላይ ሥራ ከመያዝ መከልከልህን እንዴት ታየዋለህ? የወጣቶች ፎረም በሚል የመደለያ ብር የሚሰጡህ ለእውነት ይመስልሃልን? ይህን የሚያደርጉት ዘላቂ እድልህን በጊዜያዊ ጥቅም በመለወጥ የአገርህንና የሕዝብህን እጣ ፋንታ እያበላሸ ያለውን ፖሊሲያቸውን እንድትደግፍ እየሞከሩ ስለሆነ ጠንቀቅ በል:: ከመኢአድ ጋር በመቆምም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዚህ ሁሉ ግፍና በደል ነጻ ለማውጣት ጥረትህን ጀምር።

## የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!

ዛሬ የወያኔ መንግስት ገጠሬውንም ሆነ ከተሜውን አሻንጉሊት ሊያደርግ እየሞከረ መሆኑን እወቅ፣ ሰፊ ሀገራዊ ራዕይ እንዳይኖርህ እየተደረገ በመንደር፣ በዘርና በጎሳ ከፋፍሎ የኋላ ቀሮች አስተሳሰብን እንድታራምድ የራሱን የተፅዕኖ መስመር ዘርግቶብሃል። በማንኛውም የሥራ መስክ እና ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ መለያ ምክንያቶችን በማስፋት ማንም ሰው የዘር ግንዱን ብቻ እንዲያስብ የዘር መሰሉን ብቻ እንዲቀጥር እየተደረገ ነው። ይህ አንድነትንና ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀጭጭ አስተሳሰብ በመተባበርና በመደራጀት ባስቸኳይ ልትገታው ትችላለህ ይገባሃልም።

የጋራ ሀገርህ ኢትዮጵያን ለማሳደግ የላቀ ዕውቀት ባላቸው ኢትዮጵያውያን እንዳትጠቀም በጠባብ የዘር ቀለበት ውስጥ አስገብተውህ የዘር አመለካከት ባርያ አድርገውሃል። ይሄ ደግሞ ነጣጥለው እንዲገዙህ፣ ነጣጥለው እንዲረግጡህና እንዲገድሉህ፣ ሰብአዊ መብቶችህን እንዲገፉህ አስችሏቸዋል። ይህ ሁሉ በመደራጀትና አንድ በመሆን እንደሚለወጥ ማመንና ለለውጥ መነሳት ይገበሃል። መኢአድም የዚህ ለውጥ መነሻ ነውና በሥሩ ተደራጅተህ ተከተለው
የመኢአድን ስትራቴጂ መርህ አድርገህ ስትታገል የገጠር መሬት በግል ባለቤትነት እንዲይያዝ ትታገላለህ ለድልም ትበቃለህ፣ የከተማ ቦታን ከሊዝ ነፃ በማድረግ የምታዝዝበት አንጡራ ሀብትህ ታደርጋለህ፣ ክብርና ሞገስ የሚያጎናፅፍ ልዕላዊነትህን የሚያረጋግጥ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ባለቤት ትሆናለህ፣ አገርህም ባለወደብ እንድትሆን በሰላማዊ መንገድ በመታገል የቀድሞ ታሪክህን ታስከብራለህ። ፖሊስና መከላከያ ከፓርቲ ዕዝ ውጭ እንዲሆኑ፣ የትምህርት ፖሊሲው ህዝብ መክሮ ያፀደቀው ይሆን ዘንድ ታሪክ ትሰራለህ፣ ሁሉም ብሔረሰቦች ባህላቸው፣ ቋንቋቸውና ወጋቸው ክቡር መሆኑ ታውቆ እንዲያድግና እንዲከበር ትሟገታለህ። ስለዚህ ወጣት፣ ሴት፣ ወንድ፣ አረጋዊና መበለት ሳትል ከመኢአድ ጎን በመሰለፍ ለሰላማዊ ትግሉና ለለውጥ ተነስ።

በ1997 ዓም ብሔራዊ ምርጫ ምክንያት የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት በዜጎች ላይ በፈጸመው አስከፊ በደል ተስፋ በመቁረጥም ሆነ በሌላ ምክንያት ይህን በደል በመፈጸም ላይ ያለውን የኢህአዴግ መንግሥት በምርጫ ካርድ በመቅጣት ሃላፊነትህን ሳትወጣ ቀርተህ የድሉ ውጤት እንደገና በገዘዎች እጅ ከገባ አገራችንም ሆነ ሕዝቧ በቀላሉ ሊወጡት ወደ ማይችሉት የባሰ አዘቅት ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልግሃል::

ስለዚህ አሁኑኑ በሰላማዊ ትግሉ ውስጥ ገብተህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ራዕይ እውን እንድታደርግ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ጥሪውን ያቀርበል

**መኢአድ ባለበት ሁሉ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት አለ**
**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**
**የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)**

በሊበራሊዝም ከሕግ ውጭ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነፃ ነው